# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 1 ቁጥር 42 ግንቦት 15 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## < <አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለማዳከም የሚኬድበት መንገድ ለማንም አይጠቅምም፤ የትምም አያደርስም ! > > ዋሲሁን ተስፋዬ የኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ



# ነፃ ሀሳብ

## የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ተከትሎ የታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሁኔታ እና እንዲሁም አሁን በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት 5 አመት የሥራ ዘመን መጠናቀቅ ተከትሎ ሊካሄድ የሚገባው ምርጫ ባለመካሄዱ የመንግሥት እና የፓርላማው የሥራ ዘመን እንደምን ባለ ሕገ መንግሥት መሠረት ሊረዝም ይችላል?!

አሁን ባለው እና በ1987 ዓ.ም በሥራ ላይ የዋለው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና የመንግሥት የሥልጣን ጊዜ መጠናቀቅ ሁኔታ ሲያጋጥም ምርጫ ሳያካሂድ እንደ ምን ባለ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ መታለፍ እንዳለበት በግልጽ የሕግድንጋጌ አላሰፈረም፡፡ይሁንና ይህን የሕግ ክፍተት ለመሙላት የሚያስችሉ 4 ሕገ መንግሥታዊ አማራጮች ማየት ይቻላል፡፡

ሀ. አንባቢያን እነዚህን የሕግ ድንጋጌዎች ለማገናዘብ ይረዳቸው ዘንድ በዚህ ፅሁፍ እንደ አስፈላጊነቱ የሚጠቀሱ ጠቃሚ የሕግ አንቀጾች የሚከተሉት ናቸው፡፡

አንቀጽ 58(3) የፓርላማው ሆነ የመንግሥት የሥራ ዘመን 5 ዓመት ስለመሆኑ፣
አንቀጽ 60 ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፓርላማውን ለመበተን ስለሚችሉ፣
አንቀጽ 62 የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር፣
አንቀጽ 64 የፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔዎችና የሥነ ሥርዓት ገደቦች፣
አንቀጽ82 የሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባኤ አወቃቀር፣
አንቀጽ 83 ሕገ መንግሥቱን ስለ መተርጎም፣
አንቀጽ 84 የአጣሪው ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር፣
አንቀጽ 93 ስለ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣
አንቀጽ 104 የሕገ መንግስት ማሻሻያ፣
አንቀጽ 105 (2) የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎችና ማሻሻያ ስለ ማጽደቅ፣

ለ. ችግሩን ለማለፍ

አማራጭ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎች

1 በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 60(1) መሠረት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥልጣን ዘመኑ




ከማለቁ በፊት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፍቃድ ፓርላማውን ሊበትን ይችላል፡፡ ሆኖም የተወካዮች ምክር ቤት በተበተነ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ አዲስ ምርጫ መደረግ አለበት፡፡ ይህ አማራጭ የሥራ ዘመኑ ያለቀውን መንግሥት የስድስት ወራት ተጨማሪ ጊዜ ይሰጠዋል፡፡

ይሁንና ይህ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሁኔታ በስድስት ወራት የሚወገድ መሆኑን እርግጠኛ ካለመሆናችን ባሻገር በእነዚህ ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሥራ የሚቆይ ባለመሆኑ ጠቅላይሚኒስትሩ ማናቸውንም ሕግ ማውጣት የማይችሉ በመሆናቸው ሀገሪቱ ስለሚያጋጥማት የጦርነትም ሆነ ሌሎች ያልታሰቡ ሁኔታዎች የሕግ አውጪዎችን ይሁንታ ማግኘትና መተግበር አይቻልም ማለት ነው፡፡

2. በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 93 መሠረት በተከሰተው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት መንግሥት የወረርሽኙን ስርጭት ለመግታት ይቻለው ዘንድ የአስቸኳይ ጊዜ አውጇል፡፡ ይህ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ድንጋጌ ለመንግሥት ከመደበኛ ጊዜው የበዛው በተለይ ለአስቸኳይ ጊዜ ለመቀልበስ ያመቻል ያላቸውን ሰፊ የማስፈጸም ሥልጣን ሰጥቶታል፡፡ በዚህም መሠረት በአንቀጽ 23(4)(ሐ) በግልጽ እንደሰፈረው በአንቀጽ 18፣25፣39 (የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ስያሜ፣ ኢ-ሰብዓዊ አያያዝን ስለ መከላከል፣ የእኩልነት መብትን ስለመጠበቅ እና የብሔር ብሔረሰቦች መብት እስከ መገንጠል) ከተገለጹት የመብት ድንጋጌዎች ጨምሮ ሌሎቹን የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ማገድ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

አንዳንድ የሕግ ምሁራን ይህን የሕግ ድንጋጌ ሲተረጉሙት የታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ድንጋጌ አሁን የተከሰተውን በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ምርጫ ያለመካሄድን እና በአንቀጽ 59 (3) በ5 አመት የሥራ ዘመን መጠናቀቅ ምክንያት የሚበተነውን ፓርላማ እና የመንግሥት የሥራ ዘመን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሁኔታው እስኪወገድ ተፈጻሚነቱን ሊያግደው እና ያለ ምርጫ በሥራ ላይ ሊያቆየው ይችላል የሚል የሕግ አስተያየት ያቀርባሉ፡፡

ይሁንና እንደ ፀሐፊው እምነት ይህ የሕግ አስተያየት መሠረታዊ የሕግ ክፍተት ያለበት ነው፡፡ ምክንያቱም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መጽደቅም ሆነ አፈጻጸሙ በየጊዜው በምክር ቤቱ ይሁንታ የሚፀድቅበትና ክትትል የሚደረግበት መሆኑ በሕጉ በግልጽ ተደንግጓልና፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በመራዘሙ ምክንያት በየአራት ▼



# ለመላው የዕስልምና ሃይማኖት ተከታዮች፣



እንኳን ለአንድ ሺ አራት መቶ አርባ አንደኛው፣ (1441) የረመዳን ጻምና የኢድ በዓል በሰላም አደረሳችሁ። የዘንድሮውን የኢድ በዓል የምናከብረው እጅግ አስቸጋሪ በሆነ የወረርሺኝ ሁኔታ ውስጥ ሆነን በመሆኑ፣ ወረርሺኙ ለተጎዳቸው ወገኖቻችን አላህ ብርታቱን እንዲሰጣቸው፣ ለእኛም ምህረቱን እንዲያወርድልን በመማጸን ነው። የዘንድሮውን የኢድ በዓል ምናከብረው በወረርሽኙ ምክኛት በቤታችንና አሰላጊውን ጥንቃቄው በማድረግ ሊሆን ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ በረመዳን ጻም ወቅት የጀመርነውን በወረርሽኙ ለመከላከል የሚያስፈልገው ጥንቃቄ ለማድረግ አቅም የሌላቸውን ወገኖችቻችንን የመረዳቱን ተግባር፣ ከኢዲ በዓል በኋላም አጠናክረን እንድንቀጥል አደራ እላለሁ።

ከውሰር እድሪስ፣

የኢዜማ የምርጫ ስትራቴጂና ማነጅመት ኮሚቴ ጸሀፊ፣


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች
ለማኅበራዊ ፍትህ
(ኢዜማ)

ግንቦት 15 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

▶ ወሩ ለመታደስ ህይወት ያለው ምክር ቤት ያስፈልገዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ህይወት የሚያራዝመው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ፓርላማ) የአምስት አመት የሥራ ዘመኑ እንዳለቀ በሕግ ሞቷል ወይም የለም፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሥልጣንም ሆነ ህልውና ያልሰጠው ወይም ደግሞ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህልውና ይቀጥላል ማለት ከፍ ያለ የሥነ አመክንዮአዊ ችግር ያለበት የሃሳብ አረዳድ ይሆናል የሚል እምነት የዚህ ፅሁፍ ፀሀፊ አለው፡፡ ለማንኛውም ይህ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ እንደ አንድ የችግር መፍቻ አማራጭ ቀርቧል፡፡

## 3. ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም

በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 62 (1) መሠረት የፌደሬሽን ምክር ቤት ሕገመንግሥቱን የመተርጎም ሥልጣን ይኖረዋል፡፡በዚህም መሠረት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤን ያደራጃል፡፡ ጉባኤውም በአንቀፅ 84 ሥር የተዘረዘሩት ሥልጣንና ተግባር ሲኖሩት በዚህም መሠረት ትርጉም የሚያስፈልጋቸውን ሕገመንግሥታዊ ጉዳዮች በማጣራት ሕገ መንግሥቱን የመተርጎም እና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሀሳብ የማቅረብ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

> ‹‹የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መጽደቅም ሆነ አፈጻጸሙ በየጊዜው በምክር ቤቱ ይሁንታ የሚፀድቅበትና ክትትል የሚደረግበት መሆኑ በሕጉ በግልጽ ተደንግጓልና፡፡››

የዚህ ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም አስፈላጊነት በተመለከተ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ተከትሎ የተራዘመውን የምርጫ ተግባር እና ተከትሎ የመጣውን የመንግሥት የሥራ ዘመን መጠናቀቅ አሁን ባለው ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ቀደም ብሎ ያልታሰበበትን የሕገ መንግሥታዊ መሠረት በትርጉም በማበልፀግ በስልጣን ላይ ያለውን መንግሥት የሥራ ዘመን የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታው ተወግዶ በሚካሄድ ምርጫ በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት እስኪተካ ድረስ ለማራዘም ያለመ ነው፡፡

የዚህ ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም አስፈላጊነትን የሚያቀነቅኑ የሕግ ምሁራንና ዜጎች ላጋጠመን ሕገ መንግሥታዊ ቀውስ የዚህ መፍትሔ ሀሳብ አማራጭነት መሠረቶች የሚሏቸው፡-

1. ከፖለቲካዊ ውሳኔ ይልቅ ሕገ መንግሥታዊ መሠረት ያለው የመንግሥትም ሆነ የምርጫ ጊዜ መራዘም አላስፈላጊ ንትርክን የሚቀንስ በመሆኑ፤
2. ፍትሐዊ ነፃና ገለልተኛ ምርጫ ለማካሄድ የዜጎች ጤንነት፣ ሠላምን እና የሕግ የበላይነትን የሚያስከብር ችሎታ ያለው ጠንካራ መንግሥት በማስፈለጉ፤
3. ሀገራችን የምትገኝበት ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታ የኢኮኖሚ ጥቅሟን እና ሉአላዊነቷን ስጋት ውስጥ የሚከቱ ሁኔታዎችን በብቃት የሚወጣ ጠንካራ መንግሥት የሚያስፈልግበት ወቅት በመሆኑ፤
4. በመፍትሔነት ከቀረቡት ሌሎች ሕገ መንግሥታዊ አማራጮች ውስጥ የወቅቱን የኮሮና ወረርሽኝ ችግር እና እንደ ሀገር ያጋጠመንን የኢኮኖሚ አቅም ውስንነት ግምት ውስጥ በማስገባት ወጪ እና ጊዜ ቆጣቢ የሆነውን አማራጭ መምረጥ ስላለብን፤
5. አሁን ከምንገኝበት የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ እና የምርጫ አስፈላጊነት አንፃር ሕገ መንግሥታዊ ማሻሻያ ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ፤
6. ይህን ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም አማራጭ ከሁሉም የተሻለ ቅቡልነት እንዳለው በአፅንኦት ያስረዳሉ፡፡

## 4. ሕገ መንግሥታዊ የማሻሻያ ሀሳብ ማፅደቅ

ሀ) ባጭሩ በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 104 መሠረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ተከትሎ በተራዘመው የምርጫ ሂደት ምክንያት የስልጣን ዘመኑ ያለቀውን መንግሥት ጊዜ ሊያራዝም የሚችል የማሻሻያ ሀሳብ፡-

በፌደሬሽን ምክር ቤት እና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 2/3ኛ የድምፅ ድጋፍ ወይም የፌዴሬሽኑ አባል ከሆኑት ክልሎች 1/3ኛው በአብላጫ ድምፅ የሚያፀድቁት የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሀሳብ ለሕዝብ ውይይት ይቀርባል፡፡

ለ) በአዋጅ አንቀፅ 105 (2) መሠረት ይህን የማሻሻያ ሀሳብ በፌዴሬሽን እና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች የጋራ ስብሰባ 2/3ኛ ድምፅ ድጋፍ እና በፌዴሬሽን ምክር ቤት አባል ክልል ምክር ቤቶች 2/3ኛ ድምፅ ብልጫ ድጋፍ ማፅደቅ ይቻላል፡፡

በመሆኑም የዚህ አማራጭ ሕገ መንግሥታዊ ሀሳብ ደጋፊዎች አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግሥት በሁሉም ምክር ቤቶች 2/3ኛ ድምፅ ድጋፍ ማሻሻያውን አቅርቦ እና በአጭር ጊዜ የሕዝብ አስተያየት ሰብስቦ በተጨማሪም በ2/3ኛ የክልል ምክር ቤቶች ድጋፍ አፀድቆ ሕገ መንግሥታዊ ማሻሻያ ቢያደርግ ያለ ምንም የሕግ ንትርክ ችግሩን ሊያውቀው እንደሚችል በዝርዝር ያትታሉ፡፡ ይህ የመጨረሻው አማራጭ የኢዜማ አቋም የተወሰደበት ሲሆን ዝርዝሩን ከፓርቲው የአቋም መግለጫው ይመልከቱ፡፡

ውድ አንባቢያን በዚህ ፅሁፍ የዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችንና የሕገ መንግሥታዊ የሕግ ውክልና መሠረት (Constitutional Juris Prudence) ለማካተት አልተፈለገም፡፡በዚህ ረገድ ጥያቄዎችካላችሁ ፀሐፊውን በሚከተለው የኢሜይል አድራሻቸው Yeshwasmeresha@gmail.com ማግኘት ይቻላል፡፡





# ‹‹ስለኢትዮጵያኖች በአርግጠኝነት የምናገረው ነገር ቢኖር ከውጪ ሀገራት የሚደረግ ተፅእኖ ካለ ያን ጊዜ ኢትዮጵያኖች ይህ የሉአላዊነት ጉዳይ ነው፤ ስለዚህም በማንኛውም ዋጋ ሉአላዊነታችንን ልናስጠብቅ ይገባል ብለው በአንድነት እንደሚቆሙ ነው››

ብርሀኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) የኢዜማ መሪ



የሕዳሴውን ግድብ ግንባታ በማስመልከት የሚደረገው ድርድር ወደ ዋሽንግተን ዲሲ መወሰዱ ውጤት የሚያስገኝ አማረጭ እንዳልነበርየኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) መሪ ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) ገለፁ፡፡

መሪው ይህን የተናገሩት ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስርጭት ፕሮግራም ላይ ባደረጉት አንድ ቃለምልልስ ነው፡፡ ኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ግብፅ ድርድሩን ወደ አፍሪካ ሕብረት አልያም ወደ ወንዙ ተፋሰስ ሀገራት ነው መውሰድ የነበረባቸው ሲሉ መሪው ተናግረዋል፡፡ እንደ አሜሪካ ያሉ ሀገራት ከዓለም አቀፍ ሕግ ውጪ ኢትዮጵያ ላይ ጫና በማሳደር የሌሎች ሀገራት ጥቅም እንዲከበር ያላቸው ፍላጎት መሳካት የማይችል ነው ብለዋል፡፡‹‹ኢትዮጵያኖችን የማያውቁ ሰዎች ብቻ ናቸው እንደዚህ ያለ ስህተት ሊሰሩ የሚችሉት፡፡ ስለኢትዮጵያኖች በእርግጠኝነት የምናገረው ነገር ቢኖር ከውጪ ሀገራት የሚደረግ ተፅእኖ ካለ ያን ጊዜ ኢትዮጵያኖች ይህ የሉአላዊነት ጉዳይ ነው፤ ስለዚህም በማንኛውም ዋጋ ሉአላዊነታችንን ልናስጠብቅ ይገባል ብለው በአንድነት እንደሚቆሙ ነው›› በማለት ኢትዮጵያኖች የትኛውንም ዓይነት የውጪ ሀገር ጣልቃ ገብነት የሚሸከሙበት ጫንቃ እንደሌላቸው መሪው አስረድተዋል፡፡

የአባይን ወንዝን በሚመለከትም አማራጩ መፍትሔ ኢትዮጵያ፣ ሱዳን፣ ግብፅም ሆኑ ሌሎች የወንዙ ተፋሰስ ሀገራት ይህን የጋራ ሀብት በጋራ የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ለማመቻቸትድርድር በማድረግ ወንዙን በጋራ መጠቀም እንዳለባቸው መሪው ተናግረዋል፡፡ መጀመሪያውኑ አሜሪካ የድርድሩ አካል መሆኗን አልደገፍም ነበር ያሉት ብርሀኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) አፍሪካ ሕብረት ወይም የወንዙ ተፋሰስ ሀገራት የሆኑ ሌሎች ሀገራትን በመያዝ ድርድር ማድረጉ የተሻለ ነው ሲሉ አማራጭ የሚሉትን መፍትሔ አቅርበዋል፡፡

‹‹አሜሪካንም ሆነ ማንኛውንም አካል በመጠቀም ተፅእኖ ለማድረስ መሞከር ኢትዮጵያኖች የሚቀበሉት አይሆንም፡፡ ኢትዮጵያኖች ይህን ከሚቀበሉ ቢራቡ ይመርጣሉ፡፡ ለሱዳኖችም ሆነ ለግብፆች የምናገረው ነገር ቢኖር የጀመራችሁት ድርድር አለ፡፡ ይህን ድርድር ከግብ አድርሱት ነው የምለው፡፡ ከዛ ውጪ ኢትዮጵያ ላይ በሌላ የውጪ ሀገር ጫና በማሳደር ኢትዮጵያ ጥቅሟን አሳልፋ እንድትሰጥ መሞከር የሚሰራ አይደለም›› ሲሉ መሪው ተናግረዋል።

በዋሽንግተን ዲሲ የአሜሪካ መንግሥት እና የዓለም ባንክ በተገኙበት በኢትዮጵያ፣ ሱዳን እና ግብፅ መካከል ይደረግ የነበረው ድርድርን በኋላ የአሜሪካ መንግሥት ትሬዠሪ መሥሪያ ቤት ያወጣውን መግለጫ ተከትሎ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) መግለጫው ሦስቱ ሀገራት ቀድመው ከደረሱበት ከፍትሃዊ ተጠቃሚነት መርህ ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት እንደማይኖረው መግለጹ ይታወሳል።

በወቅቱ ኢዜማ በሕዝብ ግንኙነት ክፍሉ በኩል ባወጣው መግለጫ ‹‹ይህግድብ ከጅማሬውአንስቶብዙውስብስብችግሮችየነበሩበትቢሆንም፣የኢትዮጵያሕዝብትልቅዋጋየከፈለበትእናእየከፈለበትየሚገኝምሀገራዊምልክትየሆነፕሮጀክትነው፡፡ታላቁየሕዳሴግድብለኢትዮጵያከሚያስገኘውየኢኮኖሚጥቅምበዘለለየአባይወንዝተፋሰስሀገራትንፍትሃዊተጠቃሚነትእናሉዓላዊነትንያዘለፕሮጀክትእንደሆነምእንገነዘባለን፡፡›› ብሎ ነበር። ኢዜማ በመግለጫው አባላት፣ ደጋፊዎች እና መላው ኢትዮጵያዊያን የግድቡን ሥራ እንዲደግፉ እና ለሀገራችን በጎ ለማይመኙ መሣሪያ እንዳይሆን እንጠብቀው የሚል መልዕክት አስተላልፏል።

# ‹‹አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለማዳከም የሚኬድበት መንገድ ለማንም አይጠቅምም፤ የትምም አያደርስም!››

## ዋሲሁን ተስፋዬ የኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ

አቶዋሲሁን ተስፋዬ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ናቸው፡፡ ዛሬ እንግዳችን አድርገን ጋብዘናቸዋል፡፡ ፓርቲያቸው ኢዜማ የኮሮና ወረርሽኝ ከመከሰቱ በፊት ከአደረጃጀት ጋር በተገናኘም ሲሰራ እንደነበር፣የኮሮና ወረርሽኝ ከተከሰተ በኋላ ምን እየሰራ እንዳለ፣ወረርሽኙ መከሰቱን ተከትሎ የማደራጀት ስራቸውን እንዴትና በምን መልኩ እየሰሩ እንዳሉ፣የወረርሽኙ መከሰት በሥራቸው ላይ እያሳደረ በሚገኘው ተፅእኖና የመንግሥት አካላት በፓርቲያቸው አባላትና መዋቅሮች ላይ እያሳደሩ ስለሚገኙት ጫና ጋር በተገናኘ የተለያዩ ጥያቄዎች አቅርበንላቸው ምላሻቸውን ሰጥተውናል፡፡ሙሉ ቃለ ምልልሳችንን እነሆ፡-



**የኮሮና ወረርሽኝ በኢትዮጵያ ከመከሰቱ በፊት የኢዜማ አደረጃጀት ምን ይመስል ነበር ፓርቲውስ ከአደረጃጀት ጋር በተገናኘ ሲያደርጋቸው የነበሩ እንቅስቃሴዎች ምን አይነት ነበሩ?**

እንደ ሚታወቀው ኢዜማ ባሳለፍነው ሳምንት ግንቦት 01 ቀን 2012 ዓ.ም የተመሰረተበትን አንደኛ ዓመቱን አክብሯል፡፡ ከምስረታው አስቀድሞም በዋናነት ትኩረት ሰጥቶ ሲሰራ የነበረው አደረጃጀቱ ላይ ነበር፡፡ የፓርቲው ምስረታ በተበሰረበትና ጠቅላላ ጉባኤው ከተካሄደበት ግንቦት 01 ቀን 2011 ዓ.ም ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በፊት አስቀድመን 312 የምርጫ ወረዳዎችን አደራጅተን ነበር፡፡ ከጉባኤው በኋላም የቀሩትን ምርጫ ወረዳዎች ለመሙላት ዓመቱን ሙሉ ጥረት እያደረግን ነበር፡፡ የኮሮና ወረርሽኝ ከመሰከቱ በፊትም አስቀድመን ካደራጀናቸው 312 የምርጫ ወረዳዎች በተጨማሪ 123 የምርጫ ወረዳዎችን አደራጅተናል፡፡ እነዚህ ያደራጀናቸው ምርጫ ወረዳዎች 15 ሥራ አስፈፃሚ አባላት ያሉበትና የወረዳው ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ባሉበት የወረዳ ሥራአ ስፈፃሚዎችን የሚመርጡበት የተደራጀ መዋቅር ነው የገነባነው፡፡ ጠንካራ መዋቅሮችን ነው ያደራጀነውም፡፡ በቢሮ ደረጃም 270 ቢሮዎችን በመላው ኢትዮጵያ መክፈት ችለናል፡፡ በአሁኑ ወቅት 435 የምርጫ ወረዳዎችን አደራጅተናል፡፡ እቅዳችን የነበረው ከ547 የምርጫ ወረዳዎች የቀሩንን ምርጫ ወረዳዎች የምርጫ ዘመቻው ከመጀመሩ አስቀድሞ አደራጅቶ ማጠናቀቅ ነበር፡፡ የእጩ ምልመላን ጨምሮ ለምርጫ ዝግጅት የሚሆኑ ሌሎች ክንውኖችን እያካሄድን ሳለ ነው ይህ የኮሮና ወረርሽኝ የተከሰተው፡፡

**አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች የኮሮና ወረርሽኝ ተከስቶ ምርጫው ተራዘመ እንጂ ኢትዮጵያ አስቀድሞም ምርጫ ልታደርግ የምትችልበት ሁኔታ ላይ አልነበረችም፡፡ ወረርሽኙ መከሰቱ እንደውም ፈረንጆቹ እንደሚሉት “Blessing in disguise” (በመጥፎ አጋጣሚ ውስጥ የተከሰተ ጥሩ ክስተት) ነው ይላሉ፡፡ እርስዎ ይህን አስተያየት እንዴት ይመለከቱታል?ኢዜማ ስለ ምርጫ ተዘጋጅቶ ነበር?**

ሀገራችን ለውጡ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ያለፉት ሁለት ዓመታት በብዙ ችግር ውስጥ ነው ያለፈችው፡፡ እንደሚታወቀው በየ5 ዓመቱ ምርጫ ግንቦት ላይ ሲካሄድ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ራሱን ሪፎርም እያደረገ ስለነበርና ከሪፎርም ጋር በተገናኘ በርካታ ስራዎችን ሲሰራ ስለነበር ይሄኛውን ምርጫ በታሰበለት የግንቦት ወር ማድረግ ስላልተቻለ ወደ ነሐሴ ተገፍቶ ነበር፡፡ ምርጫውን በሚመለከት እንደ ፓርቲ መጀመሪያ የነበረን አቋም ቢያንስ ለተወሰነ ጊዜ ሰላምና መረጋጋት ላይ እና የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ ላይ ነው መሰራት ያለበት የሚል አቋም ▶

▶ ነው የነበረን፡፡ ነገር ግን መንግሥት ሰላምና ማረጋጋትን ማስፈን እችላለሁ፡፡ የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታውንም ጎን ለጎን እሄድበታለሁ፤ ስለዚህም ምርጫው በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መካሄድ አለበት የሚል አቋም ያዘ፡፡ ይህን ጊዜ እኛም ለምርጫ ዝግጅት ማድረግ ጀምረናል፡፡ ለምርጫም ዝግጁ ነበርን፡፡ የምርጫ ስራን የሚያከናውኑ በርካታ ኮሚቴዎች አደራጅተንም ነበር፡፡ መዋቅሮቻችንንም ለምርጫ በሚሆን መልኩ እያደራጀን ነበር፡፡ የእጩ ምልመላዎቻችንንም አጠናቀን ነበር፡፡ ለምርጫም በሚገባ ተዘጋጅተን ነበር፡፡

**ስለዚህ ወረርሽኙ መከሰቱን እንደ መልካም አጋጣሚ አታዩትም?**

እንደ መልካም አጋጣሚ ልንቆጥረው አንችልም፡፡ የኮሮና ወረርሽኙን ተከስቶ ምርጫው በመራዘሙ የተነሳ ሀገሪቷ የገባችበትን ቅርቃር እያየነው ነው፡፡ የሕገ መንግሥት ቀውሱን ጨምሮ እዛም እዚህም ሲነሱ የምንሰማቸው ውዝግቦች ከምርጫ መራዘም ጋር የሚያያዙ ናቸው፡፡ ሀገሪቷ አይታው ወደ ማታውቀው የሕገመንግሥት ቀውስ ለመጀመሪያ ጊዜ የገባችውም ይህ ምርጫ በመራዘሙ የተነሳ ነው፡፡ስለዚህ ኮሮናን እንዴት አድርጎ እንደ መልካም አጋጣሚ መቁጠር ይቻላል?!ምርጫው በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ ቢካሄድ ጥሩ ነበር፡፡ የኢዜማም አቋም ምርጫው በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ እንዲካሄድ ነበር፡፡

**የኮሮና ወረርሽኝ ምርጫ ወረዳዎቻችሁን ለመከታተል እንቅፋት አልሆነባችሁም?**

አስቀድሜ እንደገለፅኩልህ በሙሉ አቅማችን ለምርጫ ዝግጅት እያደረግን ባለበት ጊዜ እና የምርጫ ዘመቻ ውስጥ ለመግባት ዝግጁ በሆንበት ወቅት ነው ይህ ወረርሽኝ የተከሰተው፡፡ ወረርሽኙ ከተከሰተ በኋላ በሁሉም የምርጫ ወረዳዎች ላይ የቀደመው አይነት እንቅስቃሴ ማድረግ አልቻልንም፡፡ እንዲህ አይነት ነገር ሲከሰት ያደራጀኸው የምርጫ ወረዳ መቀዛቀዝ ውስጥ መግባቱ አያጠራጥርም፡፡ አባሎቻችንም በኢኮኖሚ ረገድ እየተጎዱ ነው፡፡ ሀገር በተጎዳችው ልክ አባሎቻችንም እየተጎዱ ነው ያሉት፡፡ ወረርሽኙም መዋቅሮቻችን ላይ ብዙ ጉዳትን እያስከተለ ነው ያለው፡፡ ወረርሽኙ በቁጥጥር ስር ካልዋለ ምን ሊፈጠር እንደሚችል አይታወቅም፡፡ በምርጫ ወረዳዎቻችን ላይ ምከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ ነው ማለት ይቻላል፡፡

**እንዳሉት በመዋቅሮዎቻችሁ ላይ ጉዳት እያስከተለ ከሆነ ስራዎች እንዳይጓተቱ እና መዋቅሮችም በዚህ የተነሳ እንዳይዳከሙ በድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ በኩል ምን እየተሰራ ይገኛል?**

በድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ውስጥ ያሉ የምርጫ ዞኖችንየ ሚያስተባብሩ አባላት አሉ፡፡ በየቦታው ላይ ደግሞ የዞን አስተባባሪዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ የዞን አስተባባሪዎች ጋር ግንኙነታችንን አላቋረጥንም፡፡ አሁንም እንገናኛለን፡፡ ሶስትና አራት ሆኖ መሰብሰቡ ይቅር እንጂ የዞን አስተባባሪዎች መደበኛ ሥራቸውን እየከወኑ ይገኛሉ፡፡ በመደበኛነት የምናደርገውን የስልክ ግንኙነት አላቋረጥንም፡፡ ማዕከል ያሉ ዞኖችን የሚያስተባብሩ የድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ አባላት መደበኛ እንቅስቃሴያቸውን እያደረጉ ነው፡፡ ስልክንም ሆነ ሌሎች የቴክኖሎጂ አማራጮችን በመጠቀም ግንኙነቶች እንዲቀጥሉ አድርገናል፡፡ በኮሮና ወረርሽኝ የተነሳ አንዳንድ ምርጫ ወረዳዎች የከፈቷቸውን ቢሮዎች ኪራይ ለመክፈል እንደተቸገሩ ታዝበናል፡፡ ስለዚህም በድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ በኩል ተነጋግረን አማራጮችን እያመቻቸን ነው።

**ኢዜማ የኮሮና ወረርሽኝ ከመከሰቱ በፊት ከ400 በላይ የምርጫ ወረዳዎችን እንዳደራጀ ሲገልፅ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት የፓርቲው መዋቅርና አደረጃጀት ምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

ሁሉም መዋቅሮቻችን አሉ፡፡ በምንፈልገው ደረጃ ልንሰራቸው ያቀድናቸውን ሥራዎች ልንሰራ አልቻልንም እንጂ ሁሉም መዋቅሮቻችን አሉ፡፡ አስቀድሜም እንደገለፅኩት የተዘጉ ቢሮዎች የሉም፡፡ ነገር ግን አባላት እንደ ከዚህ ቀደሙ በየሳምንቱ ስብሰባ ማድረግ አልቻሉም፡፡ አንዳንድ ቦታዎች ላይም ጠቅላላ ጉባኤ ጠርቶ መተካት ያለባቸውን አባላት መተካት አልተቻለም፡፡ መደበኛ የሆነውን ሥራ መስራት አልተቻለም፡፡ ቢሆንም ግን አባላት በየምርጫ ወረዳዎቻቸው አንድ ሁለት እየሆኑ ሥራዎችን እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ኮሮና ወረርሽኝ በሀገራችን ከመከሰቱ በፊት እንደነበረው በከፍተኛ መነቃቃት ለምርጫ ዝግጅት እያደረግን በነበረው ደረጃ አይደለም መዋቅሮቻችን የሚገኙት፡፡

**ከአደረጃጀት ጋር በተገናኘ ሌላ አንድ ጥያቄ ላንሳልዎት፡፡ ኢዜማ ላይ ትችት የሚያቀርቡ አንዳንድ ወገኖች አንድ የሚሰነዝሩት አስተያየት አለ፡፡ ‹‹ድርጅቱ ከ400 በላይ የምርጫ ወረዳዎች አደራጅቼያለሁ ይላል፡፡ ድርጅቱ ይህን የሚጠቀመው ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ነው እንጂ እንደሚለው መዋቅሮቹ ጠንካራ አይደሉም፤ደካማናቸው፡፡ ጥቂት ቦታዎች ላይ ብቻ ነው የድጋፍ መሰረቱም ያለው››ሲሉይደመጣሉ፡፡ የእነዚህን ወገኖች አስተያየትበምንመልኩይመለከቱታል?**

ሥራውን የምናውቀው እኛ ነን፡፡ ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ብለን የምንሰራው ሥራ የለም፡፡ ባለፈው አንድ ዓመት የተሰራው ሥራ በኢትዮጵያ የተቃውሞ ፖለቲካ ታሪክ የመጀመሪያውና ትልቁ ሥራ ነው፡፡ ብዙዎቻችንም በፖለቲካ አሳልፈን የመጣን ነን፡፡ ከዚህ ቀደም እንደምናውቀውና እንዳለፍንበት ምርጫ 6 ወር ሲቀረው ነው መዋቅር የመዘርጋት ሥራ ውስጥ ሲገባ የነበረው፡፡ እኛ ከምስረታችን አስቀድመን 312 የምርጫ ወረዳዎች አደራጅተናል፡፡በአሁኑ ወቅትም ከ400 በላይ የምርጫ ወረዳዎች አደራጅተናል፡፡አይደለም 400 የምርጫ ወረዳዎች 200 የምርጫ ወረዳዎች ላይ የተደራጀ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ የለም፡፡ 270 ቢሮ አይደለም 20 ቢሮ ያለው ተቃዋሚ ፓርቲ ባለፉት 29 ዓመታት ማግኘት አትችልም፡፡ ስለዚህም የሰራነው ሥራ ፕሮፖጋንዳ ሳንጨምርበት በራሱ የሚናገር ነው፡፡ አደራጀናቸው የምንላቸው መዋቅሮች መሬት ላይ ያሉና ማንኛውም አካል ሊፈትሻቸው የሚችሉ ናቸው፡፡ አንድ ቦታ የተከማቹም አይደሉም፡፡ በመላው የሀገሪቱ ክፍል የሚገኙ ናቸው፡፡ የኮሮና ወረርሽኝ በሀገራችን ባይከሰት እኮ 547ቱንም የምርጫ ወረዳዎች አደራጅተን ወደ ምርጫ ለመግባት ነበር እየሰራን የነበረው፡፡ ያደራጀናቸው የምርጫ ወረዳዎች ብቻ ይበቃሉ ብለን እጃችንን አጣጥፈን አልተቀመጥንም፡፡ ያደራጀናቸው የምርጫ ወረዳዎች ላይ እየጨመርን ነበር እየሄድን የነበረው፡፡ ለማንም ብለን የምንዋሸው አይደለም፡፡ በተግባርም የሚፈተን ነው፡፡ ወደ ውድድር ስንገባ እጩ የምናቀርበው ካደራጀናቸው መዋቅሮቻችን ነው፡፡ የኮሮና ወረርሽኝ ከመከሰቱ በፊት እጩዎቻችንን በምን መልኩ ስንመለምል እንደነበር አንተም ተመልክተሀል፡፡ ሁሉም የምርጫ ወረዳዎች የጊዜ ሰሌዳዎች ተቀምጦላቸው በወጣላቸው የጊዜ ሰሌዳ በመንተራስ፣ እጩዎችን በወጣው መስፈርት አወዳድረውና ለይተው ወደ ማዕከል ሊልኩ ጫፍ ላይ ሲደርሱ ነው ወረርሽኙ የተከሰተው፡፡ ሁሉም መዋቅሮቻችን ይህንን ስራ አከናውነው ነበር፡፡ ይህ በተግባር የሚታይ ነው፡፡ ስለዚህ ለማንም ልንዋሽ አንችልም፡ ▶

እነደዚህ ለሚሉ አካላት (“ፓርቲው እንደሚለው ጠንካራ መዋቅር የለውም፡፡ ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ሲል ነው ይህን የሚናገረው”.....) እኛ ወጪያቸውን ችለን መዋቅሮቻችንን ልናስጎበኛቸው እንችላለን፡፡ (ሳቅ...)

**ባሳለፍነው ሳምንት ለዜጎች መድረክ ብልፅግና ፓርቲ ወረርሽኙን ለፖለቲካ ፍጆታ እያዋለው እንደሚገኝ ገልፀው ነበር፡፡ ኢዜማ ወረርሽኙን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረገው ጥረት ውስጥ የራሱን አስተዋፅኦ ለማበርከት አባላቶቹ ለበጎ አድራጎት ስራ ሲንቀሳቀሱ ከብልፅግና ፓርቲ በኩል እንቅፋት እየገጠማቸው እንዳለም ተናግረዋል፡፡ ይህ ነገር በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?አሁን ላይ የተለወጠ ነገርስ አለ?የትኛው የብልፅግና ፓርቲ አካል ነው እንቅፋት እየፈጠረ ያለውስ?**

የኮሮና ወረርሽኝ በሀገር ላይ የመጣ ችግር ነው ብለን ሁላችንም ይህን ችግር ለመወጣት እየተንቀሳቀስን እንገኛለን፡፡ ከኮሮናው ባልተናነሰ በየወረዳው ያሉ የብልፅግና ካድሬዎች መዋቅሮቻችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት ነው እያደረሱ ያሉት፡፡ አባላቶቻችን በተቻላቸው አቅም ራሳቸውን እየጠበቁና የተለያዩ የቴክኖሎጂ መረቦችን በመጠቀም ሥራዎቻቸውን ለማስቀጠል ጥረት በሚያደርጉበት ወቅት የብልፅግና የወረዳ አመራሮች ሳንካ እየሆኑብን ነው፡፡ የታወጀውን አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ምክንያት በማድረግ ከፍተኛ የሆነ ጫና እያካሄዱብን ነው ያሉት፡፡ ጫና እየተደረገብን እንዳለ ማሳያዎች አሉ፡፡ አንደኛው ማሳያ የአባላቶቻችን እስር ነው፡፡ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ምክንያት በማድረግ አባሎቻችን በብዙ ቦታዎች ላይ እየታሰሩ ነው፡፡ በከፍተኛ ሁኔታም በአባላቶቻችን ላይ ማዋከብና ማሸማቀቅ እየተደረገ ነው ያለው፡፡ ለእኛ በሚደርሱን መረጃዎች በብዙ ከተሞች ላይ ብልፅግና ፓርቲ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን እያካሄደ ነው የሚገኘው፡፡ ከተሞቹን ለመጥቀስ ያሕል ባሳለፍነው እሁድ በአርባ ምንጭ ከተማ በሚገኘው ማዘጋጃ ቤት ስብሰባ አካሄደዋል፡፡ ሀድያዞን፣ሾኔ ከተማ ላይም በተመሳሳይ ስብሰባ አድርገዋል፡፡ ሆሳእና እና ሶዶ ከተማም ብልፅግና ፓርቲ ሕዝባዊ ስብሰባ ካካሄደባቸው ከተሞች መሀል ናቸው፡፡ አማራ ክልል አነደድ ላይም ባሳለፍነው እሁድ ሕዝባዊ ስብሰባ አድርገዋል፡፡በሌላ በኩል በደብረ ብርሃን ከተማ ለሁለት ቀናት (ግንቦት 14 ቀን 2012 ዓ.ም እና ግንቦት 15 ቀን 2012 ዓ.ም)የሚቆይ ስብሰባ የብልፅግና ፓርቲ የወረዳ ካድሬዎች እንዲታደሙ ጥሪ ተደርጎላቸዋል፡፡ በዛሬው እለት (ግንቦት 14 ቀን 2012 ዓ.ም) ይህ ስብሰባ እየተካሄደ እንዳለ ለማወቅ ችለናል፡፡ስብሰባዎቹ ላይ በብዙ ቁጥር ነው ሰው እየተገኘ ያለው፡፡

> « ስለዚህ ለማንም ልንዋሽ አንችልም፡፡ እነደዚህ ለሚሉ አካላት (“ፓርቲው እንደሚለው ጠንካራ መዋቅር የለውም፡፡ ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ሲል ነው ይህን የሚናገረው”.....) እኛ ወጪያቸውን ችለን መዋቅሮቻችንን ልናስጎበኛቸው እንችላለን፡፡»

እኛ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ጠብቀን ሳለና አባላቶቻችን ሁለትና ሶስት ሆነው እንኳ በቢሮ እንዳይገናኙ ነው እየተደረገ ያለው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በደቡብ ወሎ በኩታበር የተከሰተውን አጋጣሚ ላነሳልህ እችላለሁ፡፡ የፓርቲያችን የወረዳ አመራር የሆኑት ሰዎች በአንድ የፓርቲያችን የወረዳ አመራር የሆነ ግለሰብ ፀጉር ቤት አካባቢ ሳሉ በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡ ፀጉር ቤቱ ውስጥ ፀጉር የሚሰራ ደምበኛ ስላለ ሶስቱ የወረዳ አመራሮች ከፀጉር ቤቱ ውጪ ርቀት ጠብቀው ተቀምጠዋል ፡፡ሌሎች ሰዎችም ከፀጉር ቤቱ ውጪ ተቀምጠዋል፡፡ የፀጉር ቤቱ ባለቤት የሆነው የፓርቲያችን አባልም ውስጥ ስራ ላይ ነበር፡፡ ውጪ የተቀመጡት ሶስቱን የፓርቲያችንን አባል ጨምሮ ውስጥ በስራ ላይ የነበረውን አባላችንን ፖሊስበ ቁጥጥር ስር አውሏቸዋል ፡፡ ውጪ የነበሩ ሌሎች ሰዎችን በመተው የእኛ አባሎችን ብቻ ፖሊስ መጥቶ በቁጥጥር ስር አውሏቸዋል፡፡ በቁጥጥር ስር የዋሉብን አራቱም አባሎቻችን የፓርቲያችን የወረዳ አመራሮች ናቸው፡፡

አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለማዳከም የሚኬድበት መንገድ ለማንም አይጠቅምም፤ የትምም አያደርስም! የመንግሥት አካላት ከዚህ አድራጎታቸው ሊቆጠቡ ይገባል የሚል እምነት አለን፡፡ የሚደረገውን ነገር ለሚያጤን በብዙ ቦታዎች ላይ ይህንን አዋጅ በመጠቀም ተቃዋሚዎችን እና ማዳከም የሚልስትራቴጂ ነው የተያዘ የሚመስለው፡፡

**በባሌ በቁጥጥር ስር የዋሉ አባሎቻችሁ እንዳሉ ሰምተን ነበር፡፡ በተጨማሪነትም በኩታበር የሚገኙ አባላቶቻችሁ በቁጥጥር ስር ውለው እንደ ነበርና ክስ እንደተመሰረተባቸውም ሰምተናል፡፡ በባሌም ሆነ በኩታበር በቁጥጥር ስር የዋሉት አባሎቻችሁ እንዴትና በምን መልክ ነው በቁጥጥር ስር የዋሉት?አሁንስ በምን ሁኔታ ላይ ይገኛሉ?**

በባሌ በቁጥጥር ስር የዋሉት አባሎቻችን አራት ናቸው፡፡ ከግንቦት 01 ቀን 2012ዓ.ምጀምሮእስካሁኗሰአትድረስእስርቤት ነው የሚገኙት፡፡ ከየመኖሪያ ቤቶቻቸው ነው የተያዙት፡፡ ከአራቱ መሀል አንዱ ተለቆ ሶስቱ እስር ቤት ነው ያሉት፡፡ የፓርቲው የወረዳው አመራሮች ናቸው፡፡ የጊዜ ቀጠሮ ፍርድ ቤት እየተመላለሱ ነው የሚገኙት፡፡ ሰባት ቀን የጊዜ ቀጠሮ ተጠይቆባቸዋል፡፡ ከሶስቱ በቁጥጥር ስር ከዋሉት አባላቶቻችን መሀል‹‹ትግል ▶



▶ ስዩም››የሚባለው አባላችን በከፍተኛ ሕመም ውስጥ ነው የሚገኘው፡፡ አካባቢው ላይ የሚገኘው ሆስፒታል ሕመሙ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ስለደረሰ አዲስ አበባ ሄዶ መታከም አለበት በሚል ሪፈርፅፎለታል፡፡ ይህንን የሀኪም የሪፈር ትእዛዝ ለፍ/ቤት ቢያቀርብም አዲስ አበባ መጥቶ ሊታከም አልቻለም፡፡ ፍ/ቤትም የዋስትና መብት ለትግል ስዩምም ሆነ ለሌሎች አባላቶቻችን ሊያከብር አልቻለም፡፡ በእስር ላይ በሚገኙት ሶስቱም አባሎቻችን ላይ እስካሁን ድረስ ክስ አልተመሰረተም፡፡ ፍ/ቤት እየተመላለሱ ብቻ ነው የሚገኙት፡፡ ለግንቦት 17 ቀን 2012 ዓ.ም ቀጠሮ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ቤታቸው ተፈትሸዋል፡፡ በፍተሻ ወቅት የኢዜማ አርማ፣ ሰነዶችና የአባላት ፎርሞች ብቻ ነው የተገኘው፡፡ ምንም ያገኙባቸው ነገር የለም፡፡ ለሚመለከተው አካል አሳውቀናል፡፡ ምንም መፍትሔ እያገኘን አይደለም፡፡ ከእስሩ በላይ በጣም እያሳሰበን ያለው የታሰሩበት ቦታ ነው፡፡ ከ30 በላይ ሰው ባለበት በአንድ ክፍል ውስጥ ነው የታሰሩት፡፡ እንደምናውቀው የኮሮና ወረርሽኝ በመጠጋጋት፣ በመጨባበጥና በመነካካት ነው የሚተላለፈው፡፡ ሰሞኑን የሚወጡት መረጃዎችእንደሚያመላክቱትም በፖሊስ ጣቢያ ያሉ እስረኞችና ፖሊሶች በኮሮና ወረርሽኝ ተጠቅተዋል፡፡ ከታሰሩት አባላቶቻችን ቤተሰቦች እንደምንሰማውም በአንድ ጠባብ ክፍል ውስጥ ከ30 እስከ 40 ሰው ነው ታስሮ የሚገኘው፡፡ በተለይ የታመመው አባላችን አቶ ትግሉ ስዩም በአሁኑ ወቅት መንቀሳቀስም አይችልም፡፡ የነርቭ በሽታ ነው ያለበት፡፡ የሚያንቀሳቅሱት እስረኞች ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ለወረርሽኙ የሚያጋልጥ ነው፡፡ የሚሰማን አካል ካለ እንዲያስብበትና ልብ እንዲል ነው የምንናገረው፡፡ በኩታበሩ የሚገኙ አባላቶቻችንን በሚመለከት አንድ ቀን ካሰሯቸው በኋላ በንጋታው እንዲፈቱ ነው የተደረገው፡፡ በተፈቱ በሶስተኛው ቀን አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን በመጣስ በሚል ክስ መስርተውባቸዋል፡፡ ክሱ በእጃቸው እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ የፍ/ቤት ቀጠሮ እየተጠባበቁ ነው የሚገኙት፡፡

**በእናንተ እምነት በባሌ፣ በኩታበርም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች በቁጥጥር ስር እየዋሉ የሚገኙት አባላቶቻችሁ ከኢዜማ እንቅስቃሴ ጋር በተገናኘ ነው በቁጥጥር ስር እየዋሉ ያሉት ብላችሁ ታምናላችሁ?**

ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ሌላ ምንም ነገር ሊሆን አይችልም፡፡ ከኢዜማ ጋር በተገናኘ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ጋር በተገናኘ ነው በቁጥጥር ስር እየዋሉ ያሉት፡፡ ግልፅ የሆነ የማሸማቀቅ ተግባር ነው እየተፈፀመ ያለው፡፡ ሌሎች ቦታዎችንም ልጠቅስልህ እችላለሁ፡፡ ቀደም ብዬ እንደገለፅኩልህ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁና የኮሮና ወረርሽኙን ተጠቅመው መዋቅሮቻችንን የማዳከም ስራ ነው እየሰሩ ያሉት፡፡ መዋቅሮችን ካዳከምን በኋላና ከዚህ ወረርሽኝ ከተወጣ በኋላ ወደ ምርጫ ከተኬደ እኛ ማሸነፍ እንችላለን በሚል ስሌት ነው እየሰሩ የሚገኙት፡፡ አብዛኛው ቦታ ላይ የብልፅግና ካድሬዎች ይህን እያደረጉ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ስለሚያያዝ ወላይታ ላይ የሆነ አንድ ምሳሌ ላንሳልህ፡፡ የዞኑ የፀጥታ ዘርፍ ኃላፊ የእኛን የዞን አስተባባሪ ደውሎ ወላይታ ዞን ላይ የምታወዳድሯቸውን ዕጩዎች ዝርዝር ስጠኝ ብሎታል፡፡ የፀጥታ ዘርፍ ኃላፊው ይህን ያደረገው ከአንድ ሳምንት በፊት ነው፡፡ የዞኑአስተባባሪ የእኔን ስልክ እንዲሰጠው ነግሬው የእኔን ስልክ ሰጥቶታል፡፡ እኔ ጋር ግን አልደወለም፡፡ የደሕንነት ኃላፊው ከዞኑ ዋና አስተባባሪ በተጨማሪ ምክትሉም ጋር ደውሎ ነበር፡፡ እዚህ ዞን ላይ 13 የምርጫ ወረዳዎች አሉ፡፡ 13ቱም የምርጫ ወረዳዎች ላይ የምታወዳድሯቸውን ዕጩዎቸ እነማንናቸው? ዝርዝራቸውን ስጠኝ ሲል ጥያቄ አቅርቦ ነበር፡፡ አንድ የቀበሌ ካድሬ ደግሞ ወደ ሀድያ የዞን አስተባባሪያችን በመደወል እዚህ አካባቢ ልታወዳድሯቸው ያሰባችኋቸው ሰዎች እነማን ናቸው?ብሎ ጠይቋል፡፡ ሁለቱም ቦታ ላይ የሚገኙት የፓርቲያችን የዞን አስተባባሪዎቻችን ይህ የፓርቲ ምስጢር ስለሆነ አንሰጥም ሲሉ ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህን ወረርሽኝ እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀምና መዋቅሮችን በማዳከምና ሌላው ላይ ጫና በማሳደር በምርጫ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት እቅድ እንዳለ እንመለከታለን፡፡ ይህ መንገድ ለማንም አያዋጣም፡፡ ከዚህ አድራጎት ቢቆጠቡ ነው የሚበጀው፡፡

**እያጋጠሟችሁ ያሉ መሰል ችግሮችን ለመፍታት ከመንግሥት አካላት ጋር ውይይት ለማድረግ ሞክራችኋል?**

መደበኛ የሆነ ውይይት አካሄደን አናውቅም፡፡ በኢ-መደበኛ መልኩ ግን ባለፈው አንድ ዓመት እዛም እዚህም የሚያጋጥሙ እስሮችን በሚመለከት እየተነጋገርን ፈተናል፡፡ አሁንም እንደዚህ አይነት ችግሮች ሲከሰቱ እየተነጋገርን ለመፍታት ጥረት እያደረግን ነው፡፡ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ችግሮቹ ይፈታሉ፡፡ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ግን እየተፈቱ አይደለም፡፡ ወረዳ ላይ ከሚገኙ ኃላፊዎች ጋርም ሆነ ማዕከል ከሚገኙ የመንግሥት ሰዎች ጋርእ የተደዋወልን ችግሮችን ለመፍታት ጥረት እያደረግን ነው የምንገኘው፡፡ ይሄ ግን ረጅም መንገድ የሚወስድ አይደለም፡፡ ሲስተማቲክ የሆነና ስርአት ባለው መልኩ ችግሮችን የመፍቻ መንገድ እስካልተዘጋጀ ድረስ በመደዋወል የሚደረጉ የግንኙነት መስመሮች እሳት የማጥፋት አይነት ተግባራት ናቸው ነው እንጂ ዘላቂ የሆነ መፍትሔ ያመጣሉ ብለን አናምንም፡፡ ዘላቂ የሆኑ መስመሮች ተዘርግተው ችግሮች ሲከሰቱ በአፋጣኝ ሊፈቱ የሚችሉበት መስመር መበጀት አለበት የሚል እምነት ነው ያለኝ፡፡

**መንግሥት ችግሮች ሲከሰቱ ችግሮቹን ለመቅረፍ በቂ ጥረት እያደረገ አይደለም እያሉኝ ነው ያሉት?**

በቂ ጥረት እያደረገ ነው ማለት አንችልም፡፡ ሀገሪቷን የሚመራው አንድ አካል ነው መዋቅሩ ይታወቃል፡፡ እንደዚህ አይነት ችግሮች ሲከሰቱ ወዲያውኑ ችግሮቹን መፍታት አለበት፡፡ ይህን ማድረግ ያለበትም ለእኛ ሲል ሳይሆን ለራሱ ሲል ነው፡፡ ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ቁርጠኛነኝ የሚል አካል የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት አቅም ያንሰዋል የሚል እምነት የለንም፡፡ ዳተኝነት ካልያዘው በስተቀር ችግሮቹን ለመፍታት ከባድ አይደለም፡፡ ያላቸውን መዋቅር በመጠቀም ችግሮቹን መፍታት ይችላሉ፡፡ አስፈላጊ የሚባለውን ጥረት እያደረጉ ነው ማለት አይቻልም፡፡

**በእኔ በኩል ጥያቄዎቼን አገባድጇያለሁ፡፡ በስተመጨረሻ መናገር የሚፈልጉት ነገር ካለ እድሉን ልስጥዎትና ቃለ ምልልሳችንን እዚሁ ላይ እንቋጨው፡፡**

ለምርጫ ወረዳዎች አንድ ነገር ማለት እፈልጋለሁ፡፡ ያለንበት ወቅት በጣም አስቸጋሪ ወቅት ነው፡፡ በተለይ ለኢዜማ ይህን ወቅት መሻገር በጣም ወሳኝ ነው፡፡ባለፈው አንድ ዓመት አመርቂ ውጤት አምጥተናል ፡፡ ብዙ ሥራዎችንም ሰርተናል፡፡ የሚቀሩን ሥራዎች ግን ነበሩ፡፡ እነዛን ሥራዎች አስቀጥሎ ከዚህ ወረርሽኝ መውጣትና ወደ መደበኛ እንቅስቃሴያችን መግባት በጣም ወሳኝ ነው ፡፡ እያንዳንዳችን አቅማችንና ለፓርቲያችን ያለን ቀናኢነት የሚፈተንበት ወቅት ላይ ነው ያለነው ፡፡ ያለው ነባራዊ ሁኔታ በጣም አስቸጋሪ መሆኑን ሁላችንም እንረዳለን፡፡ ስለዚህም ይሄንን ፈታኝ ወቅት በፅናትና በጥንካሬ መወጣት አለብን እላለሁ፡፡

**በጣም አመሰግናለሁ፤ አቶዋሲሁን!**

እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# በኩታበር የሚገኙ የኢዜማ ወረዳ አመራሮች ላይ ክስ ተመሰረተ
# በባሌ የሚገኙት ላይ ተጨማሪ የጊዜ ቀጠሮ ተጠይቆባቸዋል

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በባሌ የሚገኙት የወረዳ አመራሮቹ የጊዜ ቀጠሮ ሲጠየቅባቸው በኩታ በር የሚገኙት የወረዳ አመራሮቹ መደበኛ ክስ ተመሰረተባቸው፡፡

ኢዜማ በባሌና በኩታ በር የሚገኙ የወረዳ አመራሮች በቁጥጥር ስር ውለው እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡በባሌ በቁጥጥር ስር ከዋሉት አመራሮች መካከል አንዱ ሲለቀቀ ሶስቱ ግን አሁንም ድረስ በእስር ላይ እንደሚገኙ ያገኘነው መረጃ ያስረዳል፡፡ በእስር ላይ የሚገኙት ሶስቱ የፓርቲው የወረዳ አመራር አባላት ግንቦት 10 ቀን 2012 ዓ.ም ፍ/ቤት የቀረቡ ሲሆን ፖሊስ ተጨማሪ የ7 ቀን የጊዜ ቀጠሮ ይሰጠኝ ብሎ ጥያቄ አቅርቦ የነበረ ሲሆን ፍ/ቤቱ ፖሊስ የጠየቀውን የ7 ቀን የጊዜ ቀጠሮ በመፍቀድ ተለዋጭ ቀጠሮ ለግንቦት 17 ቀን 2012 ዓ.ም ሰጥቷል፡ ፡ አመራር አባላቱ ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡት የዋስትና መብት ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡ ፡ ከአመራር አባላቱ መሀከል በባሌ የኢዜማ ወረዳ አመራር የሆነው ትግል ስዩም በከፍተኛ ሕመም ውስጥ የሚገኝ መሆኑን የኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ለዜጎች መድረክ ገልፀዋል፡፡ትግል ስዩም በከተማው የሚገኘው ሆስፒታል ወደ አዲስ አበባ ሄዶ መታከም አለበት በሚል ሪፈር ቢፅፍለትም እስካሁን ድረስ ሕክምና ሊያገኝ እንዳልቻለና አሁንም ድረስ በእስር ላይ እንደሚገኝ ዋሲሁን ተስፋዬ አስረድተዋል፡፡ በአሁኑ ሰአትም አቶ ትግል ስዩም በታሰረበት የፖሊስ ጣቢያ መንቀሳቀስ እንደማይችልና በሰው ድጋፍ እየተንቀሳቀሰ እንዳለ ጠቁመዋል፡፡ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው ከታሰሩት አባላቶቻቸው ቤተሰቦች መረዳት እንደቻሉት በባሌ የሚገኙት የፓርቲው የወረዳ አመራሮች በአንድ ጠባብ ክፍል ውስጥ ታስረው እንደሚገኙና በክፍሉ ውስጥም ከ30 እስከ 40 ሰው እንደሚታሰርበት መረዳት መቻላቸውን ገልፀዋል፡፡ በዚህ የኮሮና ወረርሽኝ ወቅት ዜጎችን በዚህ መልኩ ማሰር ለቫይረሱ የሚያጋልጥ በመሆኑ የሚሰማ አካል ካለ እንዲያስብበትና ልብ እንዲል እንፈልጋለን ሲሉ ለዜጎች መድረክ ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩል በኩታ በር የሚገኙት አራት የወረዳ አመራሮች ከእስር ተለቀው መደበኛ ክስ እንደተመሰረተባቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ክስ የተመሰረተባቸው በኩታ በር የኢዜማ ወረዳ አመራሮች የሆኑት አቶ ዘሪሁን እሸቴ፣ አቶ መሠለ ይማም፣ አቶ አሕመድ ተሾመ እና አቶ ተስፋዬ ገብሬ ናቸው፡፡ አቃቤ ሕግ ተከሳሾቹ ርቀታቸውን ሳይጠብቁ ተጠጋግተው በመገኘታው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ላይ የተከለከሉ ተግባራቶችን በመተላለፋቸው በፈፀሙት ወንጀል ተከሰዋል ሲል ክስ አቅርቦባቸዋል፡፡ ተከሳሾቹ የክስ ቻርጁ የደረሳቸው ሲሆን የፍርድ ቤት ቀጠሮ በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል ፡፡

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ የክልል አመራሮቻቸው ላይ ጫናና ማስፈራሪያ እንዲሁም እስር እየተደረገ እንዳለና ይህም የሚደረገው የኢዜማን መዋቅሮች ለማዳከም እንደሆነ ከዜጎች መድረክ ጋር ባደረጉት ቆይታ ተናግረዋል፡፡ «አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለማዳከም የሚኬድበት መንገድ ለማንም አይጠቅምም፤ የትምም አያደርስም! የመንግሥት አካላት ከዚህ አድራጎታቸው ሊቆጠቡ ይገባል የሚል እምነት አለን» ብለዋል ፡፡